**ወዲያው ሊሰራጭ የሚችል**

*****ፊልሙን ዳውንሎድ ለማድረግ:**

**http://multimedia.hrw.org/distribute/bkljgpxvoq**

# የመን፡ ስደተኞች ስቃይ ባለበት ካምፕ ውስጥ ይታጎራሉ፡፡

## አዘዋዋሪዎች እና ባለስልጣናት ለሚደርሰው ጥሰት ባላቸው ሚና ተጠያቂ ናቸው፡፡

(ሰንዓ ሜይ 25፣ 2014 ዓ.ም.) ሂውማን ራይትስ ዋች ዛሬ ይፋ ባደረገው ጥናት በየመን የሚገኙ ህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች ከአካባቢው ባለስልጣናት ጋር በመተባበር አፍሪካዊያን ስደተኞችን ማቆያ ካምፖች ውስጥ አግተው እንደሚያሰቃዩቸው እና ይህንንም ድርጊት የሚፈጽሙት ከስደተኞቹ ቤተሰቦች አስገድደው ገንዘብ ለመቀበል መሆኑን ገለጸ፡፡ የማሰቃየቱ ተግባር እስከ ሞት ያደርሳል፡፡ የየመን መንግስት ጉዳዩን በጥብቅ ሊመረምረው ይገባል እንዲሁም ህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎቹ ላይ እና ይህንን ጥቃት በመፈፀም ተግባር ውስጥ የተሳተፉ የደህንነት ሃይሎች ላይ ክስ መመስረት አለበት፡፡

"'Yemen's Torture Camps': Abuse of Migrants by Human Traffickers in a Climate of Impunity," በሚል ርዕስ የወጣው የባለ 82 ገጹ ሪፖርት በአብዛኛው ከአፍሪካ ቀንድ በየመን በኩል አድርገው ወደ ሳውዲ አረብያ ለስራ ለመሄድ የሞከሩ ስደተኞች ላይ የደረሰውን ጉዳት መዝግቧል፡፡ ሂውማን ራይትስ ዋች ሃርዳህ በምትባለው በርካታ ካምፖች የሚገኙባት የድንበር ከተማ እና የፍተሻ ጣቢያዎች ህገወጥ የሰው ዝውውር እንዲያብብ የየመን የደህንነት ሃይሎች መፍቀዳቸውን እና በተወሰነ መልኩም የመንግስት ድጋፍ እንዳለበት ተረድቷል፡፡

'በድህነት የሚሰቃዩ ቤተሰቦቻቸውን አስጨንቀው ገንዘብ ለመውሰድ ሲሉ ህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች አፍሪካዊያን ስደተኞችን በማሰቃያ ካምፖች ውስጥ አግተዋል' ብለዋል የሂውማን ራይትስ ዋች የመካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ኤሪክ ጎልድስተን፡፡ 'በሃርዳህ ማሃል ከተማ ህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች በግልፅ ሰዎችን መኪና ላይ ሲጭኑ ስትመለከት ባለስልጣን አካላት አይናቸውን ወደሌላ አቅጣጫ እንዳዞሩት ይገባሃል፡፡'




በመጭዎቹ ሳምንታት የየመን ፓርላማ የስደተኞችን ጥበቃ ለማሻሻል እና ህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎችን እና ተባባሪ የመንግስት ሃላፊዎችን በቀላሉ ለመክሰስ የሚያስችል ጸረ-ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ረቂቅ ህግ ላይ ለመምከር ቀጠሮ ይዟል፡፡ የቀረበው ረቂቅ ህግ ህገ-ወጥ ሰው ዝውውርን የወንጀል ድርጊት እንደሆነ በመፈረጅ ዓለምዓቀፍ ደረጃውን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ረቂቅ ህጉ በድንበር አካባቢ ህገ-ወጥ የሰው ዝውውር እንዳይካሄድ ለመከላከል እና ለመከታተል እንዲቻል የመንግስትን አቅም ማጠንከርም አለበት ብሏል ሂውማን ራይትስ ዋች፡፡

በቅርብ ዓመታት ውስጥ ህገ-ወጥ የሰው አዘዋዋሪዎቹ ካምፖችን ገንብተዋል፡፡ አዘዋዋሪዎቹ ስደተኞች በጀልባ ተጭነው ባህር ጠረፍ እንደደረሱ ወደ ሳውዲ አረብያ ወይንም ወደ ሌሎች የገልፍ ሃገሮች ለስራ እንደሚልኳቸው ቃል በመግባት እና ክፍያ በመቀበል

ወይንም ፍተሻ ጣቢያ ላይ ከጥበቃ ሰራተኞች እና ወታደራዊ ባለስልጣናት ገዝተው ይወስዷቸዋል፡፡ በእነዚህ ካምፖች ውስጥ አዘዋዋሪዎቹ በየሃገራቸው ከሚገኙ የስደተኞቹ ቤተሰቦች አሊያም ውጭ ሃገር በስራ ላይ ከሚገኙ ጓደኞቻቸው አስጨንቀው ገንዘብ ለማስላክ ስደተኞቹ ላይ ከፍተኛ ስቃይ እና እንግልት ይፈጽሙባቸዋል፡፡

የየመን መንግስት እ.ኤ.አ በ2013 ዓመተ ምህረት ከወሰደው የተወሰነ የእስራት እርምጃ በስተቀር ባለስልጣናቱ ህገወጥ የሰው ዝውውርን ለማስቆም የሰሩት ስራ አነስተኛ ነው፡፡ ባለስልጣናቱ አዘዋዋሪዎቹን እርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል በተደጋጋሚ ያስጠነቅቋቸዋል፣ ነገር ግን ክስ ለመመስረት አልቻሉም፣ እንዲሁም ያሰሯቸው አዘዋዋሪዎችንም ይፈቷቸዋል፡፡ በተወሰኑ ሁኔታዎች አዘዋዋሪዎቹ ስደተኞቹን ይዘው እንዲያግቱ ይተባበሯቸዋል፡፡

ሂውማን ራይትስ ዋች  እ.ኤ.አ ከጁን 2012 እስከ እስከ ማርች 2014 ዓመተ ምህረት ባለው ጊዜ ውስጥ 18 ወንድ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞችን፣ አስር አዘዋዋሪዎችን እና ድንበር አሻጋሪዎችን፣ እንዲሁም ባለስልጣናትን፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን፣ ዲፕሎማቶችን፣ የእርዳታ ሰራተኞችን፣ የጤና ባለሙያዎችን እና ጋዜጠኞችን ቃለ-መጠይቅ አድርጓል፡፡

ስደተኞቹ በካምፖቹ ውስጥ የሚገኘውን የሚዘገንን ጎጂ አያያዝ ገልጸዋል፡፡ ድብደባ በየቦታው ነው ያለው፡፡ አንድ ሰው የሌላ ሰው አይን በውሃ መያዣ ጠርሙስ ተጎልጉሎ ሲወጣ ማየቱን ገልጿል፡፡ ሌላው ደግሞ በገመድ ሰቅለው እንዳሰሩት እና በብልቱ ላይ ውሃ የያዘ ጠርሙስ አስረው እንዳንጠለጠሉበት ገልጿል፡፡ ምስክሮች አዘዋዋሪዎቹ የሚይዟቸውን ሴት ስደተኞች እንደሚደፍሯቸው ተናግረዋል፡፡

አንድ ስደተኛ በአዘዋዋሪዎቹ ካምፕ ውስጥ ለሰባት ቀናት ታግቶ ቆይቷል፡፡ ‘እጆቼን በጀርባየ በኩል ወደኋላ ጠፍረው ያስሩኝ እና መሬት ላይ ያስተኙኛል፤ ከዚያ በብትር ይደበድቡኛል’ ብሏል ሰዒድ ለሂውማን ራይትስ ዋች፤ ጀርባው ላይ ያለውን በድብደባ ምክንያት የተፈጠረ መስመር በማሳየት፡፡ ‘ጠባቂዎቹ ወለል ላይ ያለን አንድ ሰው ፊቱን ሲሙቱት እና ጥርሱን ሲያወልቁት አይቻለሁ’

የእርዳታ ሰራተኞችም ለሂውማን ራይትስ ዋች እንደገለጹት በስደተኞች ላይ የሚደርስ ተደጋጋሚ የጥቃት ምልክቶችን መታዘባቸው እና ይህም ልክ በተጎጂዎቹ እንደተገለጸው ጥፍር መንቀል፣ የጆር ጫፍ ማቃጠል፣ ቆዳቸውን በብረት መፋቅ፣ አይናቸውን ጎልጉሎ ማውጣት እና አጥንታቸውን መስበር ያካትታል ብለዋል፡፡ በሃርዳህ የህክምና ተቋም የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች ተገደው በመደፈራቸው ምክንያት መቆረጥን ጨምሮ ጉዳት የደረሰባቸው፣ ተንጠንጥለው በመታሰራቸው ምክንያት አውራጣታቸው የተጎዳ፣ በሲጋራ እና በቀለጠ ፕላስቲክ የተቃጠሉ ስደተኞችን ማየት የተለመደ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አንድ አንድ ጊዜ የማሰቃየት ተግባር እስከ ሞትም ያደርሳል፡፡ አንድ ስደተኛ ለሂውማን ራይትስ ዋች እንደተናገረው ፊት ለፊቱ የአንዱ ሰው ብልት ላይ ገመድ አስረው በእንጨት ብትር እስኪሞት ድረስ እንደደበደቡት አይቷል፡፡ ሌላው እንደተናገረው ደግሞ የእሱ ቡድን የነበሩ ሁለት ሰዎችን አዘዋዋሪዎቹ በምሳር መተው እንደገደሏቸው ተናግሯል፡፡ ለሞት እስኪቃረቡ ድረስ ስቃይ ከፈጸሙባቸው በኋላ ሃርዳህ ከሚገኘው የዓለምዓቀፉ የስደተኞች ድርጅት የስደተኞች ጣቢያ አቅራቢያ ውጭ ይጥሏቸዋል፡፡

በመካከለኛው ምስራቅ ከሚገኙ ሃገራት እጅግ ደሃ በሆነችው የመን ከታገቱ ስደተኞች ቤተሰብ አስገድዶ ገንዘብ መቀበል እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ያስገኛል፡፡ ስደተኞቹ ለሂውማን ራይትስ ዋች እንደተናገሩት እነሱን ነጻ ለማስወጣት ቤተሰቦቻቸው እና ጓደኞቻቸው ከ200 እስከ 1000 የአሜሪካን ዶላር ድረስ የሚመጣጠን ገንዘብ ይከፍላሉ፡፡ ክፍያውን በተመለከተ ስምምነት ያደርግ የነበረው አዘዋዋሪ እንደተናገረው ብዙውን ጊዜ በአንድ ስደተኛ እስከ 1300 የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ ገንዘብ ከቤተሰብ ይቀበላል፡፡

የመናዊያንን እና አፍሪካዊያን ስደተኞችን የሚያጓጉዙ አዘዋዋሪዎች በፍተሻ ጣቢያዎች እና ድንበር አካባቢ እንዲያሳልፏቸው ለባለስልጣናት ጉቦ ይከፍላሉ፡፡ ሆኖም የባለስልጣናቱ ትብብር ከጉቦ መቀበል ያለፈ ነው፡፡ ወደ ሃገር በድብቅ የሚያስገቧቸው አዘዋዋሪዎች እና ስደተኞች በተመሳሳይ መልኩ እንደገለጹት በፍተሻ ጣቢያዎች የሚገኙ ጠባቂዎች በየመንገዱ ያገኟቸውን ስደተኞች ለአዘዋዋሪዎቹ በክፍያ ይሰጧቸዋል፡፡

አንድ ስደተኛ እሱ እና አንድ ጓደኛው ከማሰቃያ ካምፕ እ.ኤ.አ ኦገስት 2013 ላይ እንዳመለጡ እና የየመን ወታደሮች ሃርዳህ አቅራቢያ በሚገኝ የፍተሻ ጣቢያ መልሰው እንዳስረከቧቸው ለሂውማን ራይትስ ዋች ተናግሯል፡፡ ሁለቱን ሻይ እና ዳቦ እየመገቧቸው ፖሊሶቹ ስልክ ደወሉ፤ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁለት ሰዎች በመኪና መጥተው ሰዎቹን ለመውሰድ ለፖሊሶቹ ገንዘብ ከፈሏቸው እና ወደ ማሰቃያ ካምፑ ጭነዋቸው ተመለሱ፡፡

በዝውውሩ ሂደት ያለው ተሳትፎ ፖሊስ፣ ወታደር እና የደህንነት አገልግሎቱን ጨምሮ በሃርዳህ የሚገኙ የመንግስት የጥበቃ ሃይሎች ድረስ ያሉትን አካላት ያካትታል፡፡ አዘዋዋሪዎቹ፣ ወደ ሃገር ውስጥ በድብቅ የሚያስገቧቸው እና የየመን ባለስልጣናት የዝውውር

ተግባሩን የሚደግፉ የነበሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ባለስልጣናት ስም ዝርዝር ለሂውማን ራይትስ ዋች ሰጥተዋል፡፡ ሁለት ባልስጣናት አዘዋዋሪዎቹ ላይ እርምጃ እንዳይወስዱ እና እንዳያስሯቸው በማለት በጉቦ እንደሚደልሏቸው ተናግረዋል፡፡

ሂውማን ራይትስ ዋች ኢ.ኤ.አ በኤፕሪል ወር ለመከላከያ ሚኒስቴር መስሪያቤት ለላከው ጥያቄ በሜይ ወር የተላከ መልስ ተቀብሏል፡፡ መስሪያቤቱም በዚህ የመልስ ደብዳቤው የማሰቃያ ካምፖችን ለማጥፋት የወሰዳቸውን እርምጃዎች ዘርዝሮ ገልጿል ሆኖም በፍተሻ ጣቢያዎች የሚገኙ ሃላፊዎችን ጨምሮ በህገ-ወጥ ሰው ዝውውር ላይ የመንግስትን ተሳትፎ ክዷል፡፡ ሚኒስቴሩ በዝውውር ላይ ተባባሪ ነው የሚል ክስ ምርመራ የተካሄደበት ባለስልጣን እንደሌለም ገልጿል፡፡

ኢ.ኤ.አ ከማርች እስከ ሜይ 2013ዓ.ም. የየመን የጥበቃ ሃይሎች የአዘዋዋሪዎች ካምፖች ላይ ተከታታይ እርምጃ ወስደዋል፡፡ የመከላከያ ሚኒስቴሩ የጥበቃ ሃይሎች እርምጃቸውን ያቆሙት ስደተኞቹን ነጻ ካስለቀቁ በኋላ ምግብ እና መጠለያ ማቅረብ ስለተሳናቸው ነው ብሏል፡፡ የጥበቃ ሃይሎች እርምጃ የወሰዱባቸው አብዛኛዎቹ ካምፖች ተመልሰው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ባለስልጣን አካላት አስታውቀዋል፡፡

በሃርዳህ አነስተኛ ወንጀሎችን የሚከታተሉ አንድ ዳኛ ከስደተኞች ጥቃት ጋር በተያያዘ አንድ ጉዳይ ብቻ እንዳጋጠማቸው እና ያንም ቢሆን አቃቤ ህጉ የተሸነፈበት ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡ ሒውማን ራይትስ ዋችም በአቅራቢያ በሚገኙ የወንጀል ፍርድ ቤቶች የቀረቡ ከፍተኛ ክሶች ስለመኖራቸው ያገኘው ፍንጭ የለም፡፡ የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ባለስልጣናት አዘዋዋሪዎቹን ይተባበራሉ በተባሉ ባለስጣናት ላይ የተወሰደ አንድም የዲስፕሊን ወይንም ህጋዊ እርምጃ መጥቀስ አልቻሉም፡፡ የየመን መንግስት በስደተኞች ላይ ለሚፈጸም ከፍተኛ ጥቃት የግል አካላትን እና የመንግስት ባለስልጣናትን ተሳትፎ በተመለከተ ምርመራ አለማካሄዱ እና ክስ አለመመስረቱ የመን ቃል የገባችበትን የሰዎች የመኖር እና አካላዊ ደህንነት የመጠበቅ ዓለም ዓቀፍ ህግ የሚጥስ ነው፡፡

የሳውዲ ድንበር ባለስልጣናትም ድንበር የሚያቋርጡ ሰዎችን ይዘው መልሰው ሃርዳህ ለሚገኙ አዘዋዋሪዎች መልሶ በማስረከብ በስደተኞች ላይ ለሚደርስ ጥቃት ተሳትፎ እንዳላቸው ስደተኞች፣ አዘዋዋሪዎች እና የየመን ባለስልጣናት ለሂውማን ራይትስ ዋች ተናግረዋል፡፡

የየመን መንግስት አዘዋዋሪዎች ስደተኞችን የሚያግቱበት እና ጥቃት የሚፈጽሙበትን ካምፕ ለመዝጋት ዘርፈ ብዙ ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርበታል፤ ይህም አዘዋዋሪዎቹ እና የዝውውሩ ሂደት ተባባሪ የሆኑ ባለስልጣናት ላይ ያለምንም የደረጃ ልዩነት እርምጃ መውሰድ እና ክስ መመስረት ማካተት አለበት ብሏል ሂውማን ራይትስ ዋች፡፡ መንግስት ከሰብዓዊ ተራድኦ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ከእገታው ነጻ የተደረጉ ሁሉም ስደተኞች በቂ ምግብ፣ መጠለያ እና የጤና ድጋፍ እንዲያገኙ በጋራ መስራት አለበት፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ፣ የአውሮፓ ህብረት እና አባል ድርጅቶቹ፣ እንዲሁም ሳውዲ አረብያን ጨምሮ የገልፍ የትብብር ካውንስልን ጨምሮ ለየመን ድጋፍ የሚሰጡ ዓለምዓቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የየመን መንግስት በህገወጥ የሚንቀሳቀሱ የስደተኛ ማገቻ ጣቢያዎችን እንዲዘጋ እና ከአዘዋዋሪዎቹ ጋር የጥበቃ ሃይሉ የሚያደርገውን ትብብር በተመለከተ እርምጃ እንዲወስድ ጥሪ ማቅረብ አለባቸው፡፡

'ከፍተኛ የመስራት ፍላጎት ኖሯቸው ለድንበር አሻጋሪዎች የሚከፍሉ ሰዎች በመንገዳቸው ሁሉ እንዲሰቃዩ እና እንዲዘረፉ አይደለም የተሰማሙት፡፡' ብለዋል ጎልድስተን፡፡ 'ለትርፍ ሲሉ ስደተኞችን የሚያሰቃዩ ህገ-ወጥ ሰው አዘዋዋሪዎች እና ረዳቶቻቸውን በተመለከት የመን ምንም አይነት ትግስት ልታሳይ አይገባም፡፡'

"'Yemen's Torture Camps': Abuse of Migrants by Human Traffickers in a Climate of Impunity" በሚከተለው ሊንክ ይገኛል:

http://hrw.org/node/125458

የመንን በተመለከተ ለተጨማሪ የሂውማን ራይትስ ዋች ሪፖርት፣ የሚከተለውን ይጎብኙ:

http://www.hrw.org/middle-eastn-africa/yemen

ለተጨማሪ መረጃ በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ:

በኢስታንቡል በልኪስ ዊሌ (እንግሊዘኛ፣ አረበኛ፣ ፈረንሳየኛ፣ ጀርመነኛ) +1-917-385-4146 (ሞባይል); ወይንም ኢሜይል willeb@hrw.org. በቲውተር የሚከተለውን ይከታተሉ @belkiswille

በሰንዓ ኤሪክ ጎልድስተን (እንግሊዘኛ፣ ፈረንሳየኛ) +1-917-519-4736; ወይንም ኢመይል goldstr@hrw.org

በካይሮ ታማራ አልሪፋይ (እንግሊዘኛ፣ አረብኛ፣ ፈረንሳየኛ፣ ስፓኒሽ) +20-122-751-2450 (ሞባይል); ወይንም alrifat@hrw.org